# የትዝብት አምድ ቁጥር 11

# የአሣ ግማቱ ከጭንቅላቱ

## ኢትዮጵያዊነት ሁሉንም ይመለከታል

- **የአሣ ግማቱ ከጭንቅላቱ ፡-** ሰሞኑን የወያኔው መንግሥት በሙስና ስም በርካታ ባለሥልጣኖችን ወደ ፍርድ ለማቅረብ ጉድ ጉድ እያለ መሆኑን በብዙሃን የዜና ማሰራጫዎች እየሰማን ነው። የሚገርመው ከጥቂት ወራት በፊት በአሜሪካ ያለው የፎርብስ ድህረ-ገጽ ላይ ታትሞ የወጣው የእርግሊዝኛ መጣጥፍ ውስጥ Ethiopia's Cruel Con Game የወያኔ መንግሥት ከሥልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ በምዕራቡ ክፍለ ዓለም በዕርዳታ መልክ $30 ቢሊዎን የአሚሪካን ብር ያክል ወደ መንግሥቱ ካዝና የገባ መሆኑን ጠቁሞ $ 30 ቢሊዮን ብር ወደ ውጪ በተለያዩ ዘዴዎች በባለሥልጣናት እየወጣ መሆኑን ያመለክተናል። ታዲያ የሰሞኑ ግርግር ትናንሽ ሌቦችን ይዞ ለፍርድ ማቅረብ ሙስናን ማስወገድ አይችልም። ለምን ቢሉ የሙሥናው አናት የወያኔ ሥርዓት ስለሆነ ማለት ነው። የአሣ ግማቱ ከጭንቅላቱ ነው ስንልም የወያኔ ሥርዓት ከነ ግሣንግሡ ተመንግሎ መጣል ያለበት የገለማ ሥርዓት እሱው ወያኔው ስለሆነ።

- ## ኢትዮጵያዊነት ሁሉንም ይመለከታል፡-

<table>
<tr>
<td>
</td>
<td>ሰሞኑን ኢትዮጵያዊነት ፡- የዜጎች መብት ማስከበሪያ ጉባኤ<br>Ethiopiawinnet: Council for the Defense of Citizens' Rights የሚባለው ስብስብ በተለያዮ ርዕሶች ላይ ሕዝባዊ ውይይት ለማድረግ በራሪ አውጥቶ በዚህ ድረ-ገጽ ላይም መልዕክቱን አውጥተነዋል። በተለያዩ ርዕሶችም ላይ ብዙ ዶክተሮችን ያካተተ ውይይቱን እንደሚመሩና እንደሚያቀርቡም ያመለክታል። ብቻ ምክራችን ኢትዮጵያዊነት ሁሉንም ያመለክታልና እንዲህ ያለ ቅን የተሚላ ውይይት መሠረቱን ሰፋ ማድረጉ ጥሩ ውጤት ያመጣል እንላለን። በዚሁ ስብሰባ ርዕስ<br>REIMAGINING A NON-ETHNOCENTRIC ETHIOPIAN STATE – ROUNDTABLE [1:00 – 2:30 pm]<br>Chair: Ayalsew Dessie በሚለው የአማራ ድርጅቶች መዘርዘር ለምን ይሆን?</td>
</tr>
</table>

ይህች ልዩ አምድ በአሁኗ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን ሥርዓት አንኮታኩቱ ለመጣል ከመቼዎም የበለጠ የተነሳሳበትና ትግሉንም በሕብረ-ብሔራዊ መልክ መቅረጽን የተረዳበት ለመሆኑ በቅርቡ በሰሜን ኢትዮጵያ የተካሄዱት ሰላማዊ ሰልፎችና ሕዝባዊ አመጾች ያሳያሉ። ይህም የትግል አቅጣጫ ወያኔንና ደጋፊዎቹን፣ ተለጣፊዎቹን አስደንግጧል። የሕዝብ አመጻ እየገፋ በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ የኃይል ሚዛን ለውጥ ስለሚኖር ያንን ለመገደብ ወይም ጠልፎ ለራስ ለማድረግ በወያኔም በኩል በሁሉም የሕዝብን ድምፅ እያሰማ የሚመጣ ስብስብና ቡድን እንደ አሸን የሚፈላበት ወቅት ስለሆነ የአሲምባ አንባቢያን ግንዛቤን እንዲያገኙ አለፍ አለፍ ብለን ከድህረ-ገፆች አካባቢና ከሌሎችም ያገኘናቸውን አጠር ካለ አስተያየት ጋር የምናቀርብበት አምድ ይሆናል።

- ***ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ!***
-

| | |
|---|---|
|  | **አይታክቴው አድርባይ በየነ ጴጥሮስ የወያኔውን አባይ ጸሕዬ እጅ ጨብጦ ሲመረቅን እነሆ ። እንዲህ ዓይነት ተቃዋሚዎች ናቸው ሕዝብን ነጻ የሚያወጡት? ኸረ በሕግ አምላክ!! መልሱ ግልጽ ነው። ዋናው ጥያቄ ግን ሕዝብ አንቅሮ የተፋቸው የበየነ ዓይነት ማፈሪያዎች መቼ ነው ከፖለቲካው መድረክ የሚወገዱት የሚለው ነው ። በየነ ጴጥሮስና አሁን ውጭ ሀገር ያለ ጓደኛው የ1997ን የሙት ከተማ አድማ ከአሜሪካና እንግሊዝ ጋር ሆነው ማክሻፋቸውንና መለስን ከውድቀት ማዳናቸውን አንረሳላቸውም !!!** |

- ***ያላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል ይሏል፦** [ታማኝ በየነ የግንቦት ሰባት ምክትል ጠቅላይ አዛዥ ከወያኔ ትግሬ ጋር አብሮ ለመሥራት ይፋ አደርጓል](#) ! ታማኝ በየነ ከወያኔ ጋር መሥራት ካማረው ለምን አዲስ አበባ አይሄድም? አቦ ለቀቅ አድርገንና ሂድ። በነገራችን ላይ ሙሉውን የራዲዮ ቃለ መጠይቅ ለመስማት ከላይ የተሰመረበት ላይ ይጠቁሙና ጥያቄና መልሱን ያድምጡ።*

የኢሲምባ ድረ-ገጽ አዘጋጅ

ይህች ልዩ አምድ በአሁኗ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን ሥርዓት አንኮታኩቶ ለመጣል ከመቼዎም የበለጠ የተነሳሳበትና ትግሉንም በሕብረ-ብሔራዊ መልክ መቅረጽን የተረዳበት ለመሆኑ በቅርቡ በሰሜን ኢትዮጵያ የተካሄዱት ሰላማዊ ሰልፎችና ሕዝባዊ አመጾች ያሳያሉ። ይህም የትግል አቅጣጫ ወያኔንና ደጋፊዎቹን፣ ተለጣፊዎቹን አስደንግጧል። የሕዝብ አመጻ እየገፋ በሚመጣበት ጊዜ ደግሞ የኃይል ሚዛን ለውጥ ስለሚኖር ያንን ለመገደብ ወይም ጠልፎ ለራስ ለማድረግ በወያኔም በኩል በሁሉም የሕዝብን ድምፅ እያሰማ የሚመጣ ስብስብና ቡድን እንደ አሸን የሚፈላበት ወቅት ስለሆነ የኢሲምባ አንባቢያን ግንዛቤን እንዲያገኙ አለፍ አለፍ ብለን ከድህረ-ገፆች አካባቢና ከሌሎችም ያገኘናቸውን አጠር ካለ አስተያየት ጋር የምናቀርብበት አምድ ይሆናል።